**በግጭቶች ምክንያት ህይወታችዉን፣ ንብረታቸዉን፣ ማህበራዊ አገልግሎቶችን ላጡ እና ሰብአዊ መብታቸዉ እየተጣሰ ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ድምፅ እንሁን!**

በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማኅበራት በየጊዜው በሃገራችን በተለያዩ ቦታዎች ስለሚከሰቱ ችግሮች እና አለመረጋጋቶች ጥሪዎች እና ጋዜጣዊ መግለጫዎችን በማውጣት ተጎጂዎች አስፈላጊውን ትኩረት እንዲያገኙና ጥቃቱም እንዲቆም ድምፃቸውን ሲያሰሙ እንዲሁም የማስተባበር ስራዎችን ሲሰሩ ቆይተዋል። ከዚህም በተጨማሪ ለችግሮቹ ምላሽ በመስጠት ረገድ እስካሁን ድረስ በተለያዩ አካባቢዎች ለተጎዱ እና ለተፈናቀሉ ዜጎች በከፍተኛ ርብርብ የተቻላቸውን ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

ሆኖም፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚቀሰቀሱ ግጭቶች፣ አለመረጋጋቶች እና የሠላም መደፍረስ አሁንም በመቀጠላቸው በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት እየጨመረ ሄዷል። በቅርቡ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በተለይም በሰሜን ሸዋ በአጣዬ እና ሸዋሮቢት ወረዳዎች ሚያዝያ 10 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ፤ ብሄርን መሰረት ያደረጉ እና የአጸፋ ጥቃቶች የብዙሃን ሲቪል ሰዎችን ህይወት እየነጠቁ መሆናቸውን አሳውቋል። በተጨማሪም ሚያዝያ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በቤኒንሻንጉል ጉምዝ ክልል ከማሺ ዞን ግድያዎች እና የንብረት ውድመት፤ በጂማ ሊሙ ኮሳ ወረዳ በቀጮ ክርክራ እና ጋሌ ቀበሌ፤ በ ሚያዝያ 15 ቀን 2013 ዓ.ም በደቡብ ብሔር፣ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል አማሮ ልዩ ወረዳ ዳኖ ቀበሌ በታጠቁ ኃይሎች ስለደረሱ ጥቃቶችም በማህበራዊ መገናኛ ገፁ ገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ከላይ ከተዘረዘሩት ግጭቶች ቀደም ብለው የተከሰቱ ሌሎች ግጭቶች ይህን መግለጫ እስካወጣንበት ቀን ድረስ ተባብሰው ቀጥለዋል። በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ጉዳዬች ቢሮ (UN OCHA) ሚያዝያ 28 ቀን 2021 ዓ.ም ባወጣው ሪፖርት በትግራይ ክልል የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ገብተው እየሰሩ ቢሆንም እየቀጥለ ያለው ጦርነት አሁንም በገጠሩ አካባቢዎች እርዳታውን ለማዳረስ እንቅፋት እየሆነባቸው መሆኑን ገልጿል። በሌላ በኩል አለም አቀፉ የስደተኞች ተቋም (UNHCR) ያወጣው ሪፖርት በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን በተለያዩ ምክንያቶች እና አካባቢዎች ተፈናቅለው የሚገኙ ዜጎች ቁጥር 2.3 ሚሊዮን መድረሱን ያሳያል።

ስርአተ ፆታ ተኮር (Gender in Focus) በሚል ርዕስ የምንሰባሰብ እንዲሁም ስራዓተ ጾታ እና የሰብአዊ መብት ጉዳዬች ላይ የምንሰራ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት እና ድርጅቶች ከዚህ በፊት በሀገራችን በተለያዩ ክልሎች በሚቀሰቀሱ ግጭቶች ምክንያት ህይወታቸውን ስላጡ ሰዎች፤ ቁጥሩ እየጨመረ ስለመጣው ከመኖሪያው የተፈናቀለ ህዝብ፣ በሴቶች እና ህጻናት ላይ ስለሚፈፀመው የአስገድዶ መደፈር ጥቃት ድምጻችንን በማሰማት ለተለያዩ አካላት ጥያቄዎችን ማቅረባችን ይታወሳል። በዚህም መሰረት ለቆምንላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ለሞቱ ሰላማዊ ዜጎች፣ ለተጎዱ እናቶች፣ ቤተሰባቸውን ላጡ ህጻናት፣ ፆታዊ ጥቃት እየደረሰባቸው ለሚገኙ ሴቶች እንዲሁም ቤተሰባቸውን እና ኑሮአቸው እያጡ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ድምጻችንን ለማሰማት እና የሚመለከታቸው አካላት በአስቸኳይ ይህን አስከፊ ተግባር በማስቆም ዜጎችን እንድንታደግ ለማሳሰብ የሚከተለውን ጥሪ እናቀርባለን፡

1. ለኢትዮጵያ መንግስት፡-

የኢትዮጵያ መንግስት ዜጎችን የመጠበቅ ግዴታ ከመንግስታዊ ተግባራቱ አንዱ እና ዋነኛው ሲሆን ይህንን ለማስፈፀም የሚያስችል መንግስታዊ ስልጣን፣ መዋቅር እና አቅም እንዳለው ይታወቃል። ስለዚህም ከላይ ለተመላከቱት ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ እንጠይቃለን። ስለዚህም መንግስት እነዚህን ችግሮች በመፍታት ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ እንጠይቃለን።

- በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚከሰቱ ግጭቶች እና አለመረጋጋቶች ምክንያት ዜጎች የደህንነት ስጋት ላይ በመውደቃቸው ይህንን ስጋት ለመቅረፍ የሚያስችል ዜጎችን ከአደጋ የሚከላከል አስፈላጊው ጥበቃ እንዲሰጥ፤

- የህይወት መጥፋት፣ ንብረት መውደም እና መፈናቀል እንዲሁም በሴቶች ላይ የሚደርሱ የፆታ ጥቃቶች

የሚያስከትሉ ችግሮችን አስመልክቶ ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጥ፣ እንዲሁም ተጎጂ የህብረተሰብ አካላት ተጨማሪ ጥቃት እንዳይደርስባቸው አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ፤

- በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች ግጭቶች ሲከሰቱ የንፁሃን ዜጎችን ህይወት ለመንጠቅ እና ንብረት ለመውደም ምክንያት ከመሆናቸው በፊት ሰላማዊ የግጭት መፍቻ ስልቶችን ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲዘረጋ፤

- ለግጭቶች ምክንያት የሚሆኑ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ወደግጭት ከማምራታቸው አስቀድሞ መንግስት ትኩረት ሠጥቶ ለዜጎች ጥያቄ ወቅታዊ ምላሽ እንዲሰጥ፤

- በጊዜያዊ መጠለያ ቦታዎች መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር የምግብ፣መጠለያ እና እንዲሁም በተለይ ለሴቶች እና ህፃናት የሚሆኑ ድጋፎችን ሰብአዊ ድጋፎች ማቅረብ ባልተጀመረባቸው ቦታዎች ማቅረብ እንዲጀመር እንዲሁም በተጀመረባቸው ቦታዎች ደግሞ በአግባቡ እንዲዳረስ፤

- በተጨማሪ የሚደረጉ ድጋፎች ስርዓተ ፆታን ያማከሉ እንዲሆኑ በተለይም የሴቶች እና ህጻናት ልዩ ፍላጎቶችን የሚመልሱ መሆናቸውን እንዲያረጋገጥ፤

- አካል ጉዳተኛ ሴቶች እና ህፃናት አብዛኛውን ጊዜ በተለይ በአለመረጋጋት እና በግጭት ወቅት በይበልጥ ተጋላጭ እና ተጎጂ በመሆናቸው መንግስት በእርዳታ አሰጣጥ ሂደት ለእነዚህ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለየ አትኩሮት እንዲሰጥ፤

- በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ውስጥ እየተከሰቱ ያሉ የተለያዩ ግድያዎች እና በዜጎች ላይ እተፈፀሙ ያሉ አስከፊ ድርጊቶች ላይ ገለልተኛ ምርመራ ለማድረግ እንዲፈቅድ፤

- ግጭት በሚከሰትባቸው አካባቢዎች ላይ ተገቢውን የሰብአዊ እርዳታዎችን በማሰባሰብ ለሚለግሱ የሲቪል ማህበራት እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ያሰባሰቡትን ድጋፍ ለተጎጂ ማህበረሰብ በቀጥታ እንዲያዳርሱ የሚያስችል በቂ የደህንነት ጥበቃ እንዲያደርግ፤

2. ለሲቪል ማህበራት እና ድርጅቶች፡-

ሲቪል ማህበራት በዋናነት የሚቋቋሙት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን መብት ለማስጠበቅ፣ እንዲሁም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማስቻል፣ የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ ለመከላከል እና ለመጠበቅ፣ ተጥሰው ሲገኙ ደግሞ ህብረተሰቡን ወክለው ድምፅ ለማሰማት እና ጥብቅና ለመቆም ነው። ስለዚህም ሲቪል ማህበራት መብቱን ለማስከበር ለቆሙለት እና ፕሮጀክት ቀርፀው ከድህነት ለማላቀቅ እና መብቱን ለማስከበር ለሚቆሙለት ማህበረሰብ ይሕን የመሰለ ከፍተኛ ጉዳት ሲደርስበት ድምፃቸውን የማሰማት ሃላፊነት አለባቸው። ስለሆነም ለሲቪል ማህበራት የሚከተለውን ጥሪ እናቀርባለን፡-

- በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ ስፍራዎች እየተካሄደ ያለው የሰላማዊ ዜጎች መገደል እና ሰቆቃ፣ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን አስገድዶ መድፈር እና ሌሎች ፆታዊ ጥቃቶች፣ በታጣቂ ሃይሎች የሚፈፀም ጥቃት፣ የህብረተሰቡ ከቀዬው ያለፍላጎት መፈናቀል፣ የህፃናት ያለቤተሠብ መቅረትና ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች መጋለጥን እንዲሁም የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች መጥፋት በማስመልከት ድምፃቸውን ለሚመለከታቸው አካላት በተገቢው ሁኔታ እንዲያሰሙ፤

- ግጭቶች ላስከተሉት ጉዳት ምላሽ ለመስጠት በገንዘብ እንዲሁም በአይነት ሊቀርቡ የሚችሉ

ድጋፎችን ማስተባበር ላይ ከመደበኛ ስራቸው በተጨማሪ ትኩረት በመስጠት እንዲረባረቡ፤

- ጉዳት ለደረሰባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ምላሽ በመስጠት፤ ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች የማገገሚያና መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ እንዲያደርጉ፤ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ለሚፈልጉ ዜጎች እርዳታዎችን፣ ለሴቶች የሚያስፈልጉ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን እና የህጻናት ምግቦችን ጨምሮ አስፈላጊውን እርዳታ እንዲያቀርቡ እንዲሁም፤

- ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች ለደረሰባቸው ሴቶች እና ህፃናት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኙበትን ተቋማዊ ስርአቶችን እንዲዘረጉ፤

- በዜጎች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የሲቪል ማህበራት የሚቋቋሙበትን ወገንተኛ ያልሆነ አላማ ለማሳየት የሚያስችል ሚዛናዊ እና ምክንያታዊ እርምጃ እንዲወስዱ፤

- ዜጎች ላይ የሚፈፀሙ ሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርጉ፣ መረጃዎችንም እንዲያጠናቅሩ እንዲሁም አስፈላጊ የግፊት፣ የጥብቅና እና የጉትጎታ ስራዎችን እንዲሰሩ፤

3. ለአለም አቀፍ እና ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች፡-

- አስቸኳይ የምግብ፣ ውሃ፣ የመጠለያ እና ሌሎች ንፅህና መጠበቂያ እንዲሁም የህክምና ቁሳቁሶችን፣ የማማከር እና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ፤

- ከሌሎች ሃገር በቀል የሲቪል ማህበራት ጋር በመተባበር የሰብአዊ ድጋፉን ዘላቂነት እና ውጤታማነት እንዲያረጋግጡ፤

- ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ቀደም ሲል ለሌሎች የልማት ስራዎች ማስፈጸሚያ የታቀዱ የገንዘብ ድጋፎችን ወደ አስቸኳይ ድጋፎች እንዲዛወሩ በማድረግ ተጎጂው ህብረተሰብ በአፋጣኝ ድጋፍ የሚያገኝበትን መንገድ እንዲያመቻቹ፤

4. መገናኛ ብዙሃን፡-

- በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት በአግባቡ በመዘገብ አጀንዳው ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ በትክክል እንዲዘግቡ እንዲሁም አዘጋገባቸው ማስረጃን መሰረት ያደረገ እንዲሆን፤
- ጉዳዩ ተገቢውን ምላሽ ከህብረተሰቡ እና ከተለያዩ አካላት እንዲያገኝ አጥብቀው እንዲሰሩ፤

5. ሌሎች በግጭቱ ሚና ያላቸው አካላት፡- የሰላማዊ ዜጎችን ደህንነት ከሚፃረር፣ መፈናቀል እንዲሁም የህይወት መጥፋት ከሚያስከትል ተግባር እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን።

በአጠቃላይ ሰው ክቡር ነው ስለዚህ በምንም መልኩ መብቱ ሊገፋ አይገባም። በተለይ በአሁኑ ወቅት የሰውን ክብር ሙሉ በሙሉ የጣሱ ተግባራት በግልፅ በተደጋጋሚ እና በስፋት መካሄዳቸው ሁላችንም ሊያሳስበን ይገባል። ስለዚህም ከላይ ለተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት በሀገራችን እየቀጠለ ያለውን የሰው ልጅ ሞት፣ ስቃይ፣ ፆታዊ ጥቃት ፤ስደት እና ፍርሃት በአፋጣኝ እንዲቆም ሁላችንም የበኩላችንን እንወጣ!

**ስርአተ ፆታ ተኮር መድረክ አባላትና ሌሎች ሲቪል ማህበራት**
**ግንቦት 2013 ዓ.ም**

**List of CSOs:**

1. Action Aid
2. Civil Society Support Programme Phase Two (CSSP2)
3. Ethiopian Women Lawyers Association(EWLA)
4. Family Service Association (FSA)
5. Forum for African Women Educationalists (FAWE)
6. Gate for Opportunity (GO)
7. Live Addis
8. Mujejeguwa Loka Women Development Association (MLWDA)
9. Network of Ethiopian Women's Associations (NEWA)
10. New Millennium Women Empowerment Organization (NMWEO)
11. NNPWE
12. Organization for Girls, Adults and Advocacy (OGAA)
13. PELUM Ethiopia Consortium
14. PHE-Ethiopia Consortium(PHEEC)
15. Quman Women Development Association (QWDA)
16. Rooci Wadu Rohi Weddu Pastoral Women Development Organization
17. Save the Children
18. Siiqqee Women's Development Association
19. Tarkanfi Sustainable Development
20. TIMRAN
21. TIRET
22. Voluntary Service Overseas (VSO)
23. Women Can Do It (WCDI)

actionaid

CSSP2
Civil Society Support Programme
Phase 2
Partnerships supporting people

Ethiopian Women Lawyers Association

FAWE - Ethiopia Chapter

NMWEO
Empowering Women | Inspiring Success

PHE
ETHIOPIA
consortium

ROOCI WADU

NEWA

Quman Women Development Association

Save the Children

WCDI

VSO

ጥረት TIRET